# ትዝብት ቁጥር 14

ታህሳስ 30 ቀን 2004 ዓ.ም.(09-01-2012)

## አልሸሹም ዘወር አሉ

ሰሞኑን በልዩ ልዩ ድህረገጾችና ዜና አውታሮች ሲራገብ የከረመው ወሬ የኦነግ አባላት ከነበሩት መካከል እራሳቸውን በማግለል ድርጅቱ ይገፋ የነበረውንና በዓላማ ደረጃ የተመሠረተበትን የመገንጠል ዓላማ እንቃወማለን ፣በአንድነት ከቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር በመታገል በሥልጣን ላይ ያለውን የወያኔ መንግሥት ጥለን የኦሮሞ ሕዝብና የቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ የራሱን ዕድል እራሱ ሊወስንበት የሚችልበትን የዲሞክራሲ ሥርዓት ለማስፈን እንታገላለን በማለት ያወጡትን መግለጫ በሚመለከተው ዙሪያ ነበር።እንደሚታወቀው ኦነግ ለአለፉት 30 ዓመታት የኢትዮጵያ ሕዝብ አንዱ አካል የሆነውን የኦሮሞ ብሔር ተወላጅ ኢትዮጵያዊ አይደለም፤ኢትዮጵያ የምትባልም አገር ከመቶ ዓመት በፊት አልነበረችም፤የኦሮሞ ሕዝብ አገርና ነጻነቱን በአማራው ብሔር ተገፎ በቅኝ ግዛት ሥር የኖረ ሕዝብ ነው።ስለሆነም እንደተቀሩት የአፍሪካ ሕዝቦች ዳር ድንበሩ ተከብሮለት በነጻነት መኖር ያለበት ሕዝብ ነው፤ትግሉም ለነጻነት የሚያበቃ ትግል ነው በማለት በውስጥና በውጭ በጸረ ኢትዮጵያ ሃይሎች ድጋፍና አነሳሽነት ሲንቀሳቀስ የኖረ ድርጅት ነው።

በተደጋጋሚ በተለያየ ጊዜ በጸረ ኢትዮጵያነት የተነሱና በሕዝባዊ ትግል ስም የተንቀሳቀሱና በመንቀሳቀስ ላይ ያሉ ድርጅቶች ለስልጣን ያልበቁት ብቻ ሳይሆኑ በሥልጣን ላይም የወጡና አሁንም ስልጣን ለመያዝ ወዲያ ወዲህ የሚሉትን ድርጅቶች ሁሉ ያጠቃልላል።አንዳንዶቹ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አሳቢና ተቆርቋሪ መስለው የጸረ ኢትዮጵያ ሃይሎችን ተልእኮ ለማሟላት ድጎማ እየተደረገላቸው በማሳሳት ላይ ሲገኙ ሌሎቹ ደግሞ ቁልጭ ያለ የማያሻማ ጥላቻና ጸረ ኢትዮጵያ የሆነ ትግል በይፋ ሲገፉ ይታያል።እነዚህ ሁለቱ ዓላማቸው የተለያየ የሚመስል ግን በጸረ ኢትዮጵያዊነትና ለባዕድ አሽከርነት ስለተሰለፉ በመደጋገፍ ተልእኮአቸውን ለመሟላት ግንባር ፈጥረው በመንቀሳቀስ ላይ ናቸው።ስብሰባም እያዘጋጁ በተለይም በውጭ የሚኖረውን ኢትዮጵያዊ ለማዘናጋትና ውዥንብር ውስጥ ለመክተት በስፋት እየጣሩ ነው። ሙከራቸው የሰመረላቸው ይመስላል።በአንዳንዶቹም የዜና ማሰራጫና መገናኛ መድረኮች ጉሮ ወሸባይ እየተባለ ከበሮ ሲጎሰም፣እምቢልታ ሲነፋ ይሰማል። ሙሉ ለሙሉም ባይሆን በአንዳንዶቹ ቀናና የዋህ ኢትዮጵያውያን ዘንድ ተቀባይነት እያገኘ ገንዘቡንና ድጋፉን ለመስጠት ቃል እየገባና እያጨበጨበ እንዲቀበል፣እንዳይጠይቅና እንዳይጠራጠር፣ በጭፍን እንዲቀበል እየተገደደ ነው።በድፍረት የጠየቀውና ሂደቱን የተገነዘበው ደግሞ የወያኔና ያረጀው ሥርዓት ደጋፊ እየተባለ ድምጹ እንዳይሰማ በመደረግ ላይ ነው። የሁለቱም ዓላማ ኢትዮጵያ በነጻነትና በአንድነት ተከብራ ሊያኖራት የሚችለውን ፣የዲሞክራሲ ሥርዓት ለማምጣት ሳይሆን በሥልጣን ላይ ያለው የነሱው ቢጤ ጸረ ኢትዮጵያ የሆነውን የወያኔ መንግሥት አሶግዶ አምኖበትና ተዘጋጅቶበት፣ሕጋዊ አንቀጽ አውጥቶለት ግን   በተግባር ያልገለጸውን ያገር መበታተን

ሂደት ለማፋጠንና በተግባር ለመተርጎም ነው።እነዚህ በልዩ ልዩ ስምና ክልላዊ ጥቅም የተደራጁ ድርጅቶች በውጭ ሃይል አነሳሽነትና ድጋፍ የተመሰረቱ ናቸው ሲባል እንዲሁ ስም ለማጥፋት፣ትግላቸውን ለማራከስና ለማጉደፍ ሳይሆን ከተጨባጭ የታሪክ ሰነድ በቀረበ ማስረጃ በመነሳት ነው።ሰነዱ የተገኘው በኮሞዶር ጣሰው ደስታ በተጻፈው የኢትዮጵያ አንድነት ትዝታና ትግል ከሚለው መጽሃፍ ሲሆን ሰነዱ የቀረበውና የተተረጎመው ቀደም ሲል በአቶ ግደይ ባሕረሹም በጻፉት "አሞራ" ከሚለው መጽሃፍ የተወሰደ ነው።የሰነዱ ይዘት የቀድሞው የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩት ሄንሪ ኪሲንጀር የተባሉት ባለሥልጣን ለመንግሥታቸው በአፍሪካ ቀንድ በተለይም በኢትዮጵያ መከተል የሚኖርበትን ፖሊሲ በመንደፍ ያሳሰቡበትና በተግባርም የገለጹበት መመሪያ ነው።ከአሜሪካ በፊት እንዲሁ ተመሳሳይ መመሪያ በመንደፍና በተግባርም በመግለጽ የእንግሊዝ፣የጣሊያንና የፈረንሳይ መንግሥታት የቀደሙ ቢሆኑም በስልሳዎቹ መጨረሻና በሰባዎቹ መግቢያ ላይ በመስፋፋት ላይ የነበረው የሶሻሊስት ንቅናቄና የራሽያ ተጽእኖ ማየል የከባቢው የጂኦ ፖለቲክስ ሂደት የምዕራቡን በተለይም የአሜሪካንን መንግሥት አሳስቦትና አስጨንቆት ነበር።በተለይም የአረቦች እንቅስቃሴ ለ"እስራኤል"መኖር አደገኛ አዝማሚያ እየያዘ ስለመጣ በቅርብ በቁጥጥራቸው ሥር የወደቀ፣ እንደልባቸው የሚያሽከረክሩት ደካማ፣መንግሥት እንዲኖር ፍላጎታቸው ነበር፤አሁንም ነው።ለተሟላ ግንዛቤ በቅርቡ ያገኘሁትን የታሪክ ሰነድ ከዚህ በታች አቅርቤዋለሁ።ያለፈ ታሪክ ነው ተብሎ እንዳይታይ አሁንም በገሃድ የሚታይ ችግር መሆኑን ተገንዝቦ፣እንዳለፈው ጊዜ ተመሳሳይ ስህተት እንዳይደገምና ሳንዘናጋ ተባብሮ በአንድነት በመቆም አደጋውን ለማክሸፍ መነሳት እንደሚኖርብን ከወዲሁ የሚያሳስበንና የሚያስጠነቅቀን መልዕክት ነው።

በተጨማሪም ሰነዱን አውጥቼ በመለጠፉ ላይ የቅደም ተከተል ችግር ስለተከሰተና ለማስተካከል ስለተሳነኝ በገጽ አራት ላይ የሰፈረውን ወደ ገጽ አምስት የገጽ አምስቱን ደግሞ ወደ ገጽ አራት በማንሸራሸር እንድታነቡት ለማሳሰብ እወዳለሁ።በኔ በኩል ያልተሟላውንና የተፈጠረውን ችግር የተሻለ እውቀት ያለው ያስተካክለዋል የሚል እምነት አለኝ። ስለግድፈቱ ይቅርታ እጠይቃለሁ።

ሠረት ስለመሆኑና የኢትዮጵያውያንም ባህሪና ጠባይ ለሚለያዩንና እርስ ርስ ለሚያጣሉን ምቹ መሆኑን ጭምር አቶ ግደይ ባሕረሹም "አሞራ" ተባለው መጽሐፋቸው በሚከተለው ዓይነት አገላለጽ ጥሩ አድርገው ቀርበዋል። (ነፃ ትርጉም)፤

"ኢትዮጵያ ሰላም ከአገኘች አንድ ቀን ታድጋለችና፤ ሕዝቧ ሠራተኛና ታታሪ ስለሆነ፤ በዓለም ብድር እዳም እንደ ሌሎቹ ሦስተኛ (ስሉስ) አገሮች፤ ተዘፍቃ አታውቅምና፤ ለወደፊቱ ራስዋን የቻለችና የኮራች አገር ናት። እድል ስታገኝ ከሥልጣኔዋ በኋላ የምትቻል አገር አይደለችም። ስለዚህ ከንጉሥ ኃይለ ሥላሴ በኋላ ኢትዮጵያን የሚመራ መንግሥት ሰላም እንዳይኖርና፤ ኢትዮጵያም እንደ አረብ አገሮች ተከፋፍላና ተነጣጥላ ከአልተበታተነች በስተቀር፤ ለወደፊቱ በቀይ ባሕር በር ላይ አሜሪካ የምትጫወተው የኢኮኖሚ ሚና፤ የመነመነ እንዳይሆን ማደግ ከማይገባቸው፤ የቀይ ባሕር አዋሳኝ ታዳጊ አገሮች አንዷ እትዮጵያ ስለሆነች፤ እንኳንስ ከጎረቤትዋ ከሱማሊያ ጋር ቀርቶ፤ ክፍለ ሃገሮችዋን ሰሜንና ደቡብን ከፋፍሎ፤ መንግሥታችን የደከመውን ወገን በመርዳት፤ የአላመጸውን ጎሳ በማሳመጽ ዳር ድንበሩ ዘላለም ሁከትና ጦርነት እንዳይለያት፤ አድራጎት ፀረ መንግሥት ተዋጊዎችን፤ "በሰ አይ ኤ" እያደራጀን ኢትዮጵያን ሰላም በመንሳት፤ የቀይ ባሕርን ወተት የአረብ አገሮችን ነፃጅ፤ ያለ ቀረጽ አናልበዋለን።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠንካራና ብርቱም ቢሆንም ቀሉ፤ በሥልጣን ፍላጎቱ፤ ደካማ ጎን ስላለውና፤ አንዱ በሌላው ላይ ለመንገሥ ምኞቱ ስለሆነ፤ ከታሪካቸው ዲሞክራሲያዊ መንግሥት መሥርተው ስለማያውቁ፤ ድሮም ቢሆን አንዱ ንጉሥ ሌላውን በመግደል ሥልጣን መቀማትና ማመጽ ባህላቸው፤ ልማዳቸውና ታሪካቸውም ስለሆነ፤ እኛ የአሳደግነው ውሻም ሊነክሰን ሲሞክር በማስገልበጥ፤ አንዲት ዘመን በኢትዮጵያ ምድር ሰላም ሳትኖር፤ ሰሜናዊ፤ ደቡባዊ፤ ኤርትራ፤ ትግሬ፤ አማራ፤ ኦሮሞ፤ እየተባባሉ እርስ በእርሳቸው ሳይስማሙ ለረጅም ጊዜ ከኖሩ፤ ለአሜሪካ መንግሥት የቀይ ባሕር ጠቃሚ በር ነው።

ሱማሊያና ኢትዮጵያ ሰላም ሆነው አንድ ቀን ከተባበሩ፤ የአሜሪካ ትምክህትና ብልጽግና በቀይ ባሕር በርና፤ በዓለም ፊት አይኖርም።

ከዚህ በላይ የቀረቡት ነጥቦች ዋሽንግተን ወያኔንና ሻዕቢያን ወገኖ በውስጥ ጉዳያችን ጣልቃ በመግባት ያራመደው ፖሊሲና ያካሄደው ተንኮል ኤርትራን ከኢትዮጵያ እንድትገነጠል፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለአንድ ትውልድ እንዲንበረከክና ብሄራዊ መብቱን እንዲገፈፍ በቂም በቀል በትር ያለአግባብ እንዲደበደብ፣ በሕዝቡ መካከል የጎሳ መርዝ እንዲዘራ የብሄራዊ እርቅና ሰላም ዕድላቸው እንዲበላሽ ወሳኝ ሚና የተጫወተ መሆኑን ያስረዳል፡፡ በተጨማሪም ኢደጋቀ ኢትዮጵያ ከላይ ከተጠቀሱት ሁኔታዎች ውስጥ እንዳትወድቀ ሰላማዊ ሽግግር ሰፍኖ የሕዝቦቿ ደሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብት ተከብሮላቸው እፎይታ እንዲያገኙ በማሰብ ያደረገው ጥረት ሁሉ እንዲሰናከልና ፍሬ እንዳያፈራ ብሄራዊ የደሞክራሲ መብቱን ጨርሶ እንዲነፈግ ረድቷል። በዚህ የታሪክ ወቅት የአሜሪካን መንግሥት በኢትዮጵያ ሕዝብ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ በመግባት በኢትዮጵያና በሕዝቦቿ ላይ ያደረሰው ታላቅ ጉዳት የጠላትነትን እንጂ የወዳጅነትን መንፈስ ያዘለ ባለመሆኑ ታሪክ ዘወትር ሲያስታውሰውና ሲተቸው የሚኖር ጉዳይ ነው።

የአሜሪካ መንግሥት በውስጥ ጉዳያችን ጣልቃ በመግባት የሚያራምደው ፖሊሲ ዶክተር ሄንሪ ኪሲንጀር ከሃያ ዓመታት በፊት ስለቀይ ባሕር እስትራተጂክ ጥቀም ጥናት አድርገው ለመንግሥታቸው ባሳሰቡት

ክህደት የተመላበት ወንጀል ነው።ሕዝብ ተባብሮ እንዳይቆም፣ የጋራ ችግሩን በጋራ እንዳይወጣ፣የጋራ ጠላቱን በጋራ ክንድ መክቶ እንዳይመልስ ተዳክሞና እርስ በርሱ ተላልቆ በባዶ ቤትና በተዳከመ ሕዝብ ትከሻ ላይ የውጭ ወራሪዎች ገብተው የፈለጉትን እንዲያደርጉ ዕድልና በር የሚከፍት አካሄድ ነው።

ለመሰሪ የውጭ ጠላቶች ተንኮል መሣሪያ በመሆን በየአቅጣጫው በብሔር ጭቆና ስም ከሚንቀሳቀሱት ድርጅቶች አንዱ ኦነግ ነው።ይህ ድርጅት ለአለፉት ሰላሳ ዓመታት ባካሄደው ትግል እንደመሰል ድርጅቶች እንደ ኤርትራ ነጻ አውጭ ግንባርና እንደትግራይ ነጻ አውጭ ግንባር ለብቻው የሥልጣን ባለቤት ባይሆንም ደባል ሆኖ ነበር።በሥልጣን ክፍፍልና በግዛት ጥያቄ አለመግባባት የተነሳ እራሱን ከሸርክናው አሶግዶ ትግሉን ለመቀጠል በመወሰኑ ተመልሶ ጫካ ገባ።

የሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍላጎት በሰላምና በአንድነት አብሮ ለመኖር ነው።አብሮ በመኖር እውቀትና ጉልበቱን አቀናጅቶ ተፈጥሮ ያደለውን ጸጋና ሃብት እየተጋራ በመሥራት ኑሮውን ለማሻሻል፣ከድህነትና ከስደት ተላቆ መኖርን ይሻል፣ይመኛል። የሌላው ዓለም ሕዝብ ከደረሰበት የእድገት ደረጃ ላይ ለመድረስ እንጂ በድህነት ተመጽዋች እየሆነ መኖርን አይመርጥም። የሴሜኑም፣የደቡቡም፣የምሥራቁና የምዕራቡ ያገሪቱ ክፍለ አገር ሕዝብ፣ምኞትና ፍላጎቱ ይኸው ነው።ይህን ፍላጎቱን በተግባር እንዳያይ ደንቃራ መፍጠር የጠላቶቹ ዘዴ ነው።የወገኑ መስለው በማሳሳት እዛው አሮንቃ ውስጥ እንዲንከባለል ልዩ ልዩ ብልሃት ይዘው ብቅ ይላሉ።የወያኔ መንግሥት በሕዝብ የተጠላና የተወገዘ ስለሆነ ሌላ አማራጭ ለመፍጠር ይገደዳሉ።በተለይም በአረቦችና በሰሜን አፍሪካ አገሮች የተቀሰቀሰው ሕዝባዊ ተቃውሞና አመጽ በሌላው አገር እንዳይነሳ የሚያግዱበት ዘዴ ወይም በጥገና ለውጥና በተተኪ ሃይል ቁጥጥራቸውን የሚከላከሉበት ዘዴ ለመፍጠር ይገደዳሉ።ምን ግዜም ቢሆን በአንድ ብቻ ተማምነው አይቀመጡም።ሁለት ባላ ትከል የሚል መመሪያ አላቸው።

የተገንጣይ ቡድኖችም በሚደርስባቸው ክስረት፣ የዓለም ሕዝብ አመለካከት ለውጥና በተለይም የወጣቱ ትውልድ ፍላጎት ከኋላ ቀር ክልላዊ ስሜት የዘለለና የላቀ በመሆኑ አልፎ አልፎ የስልትና የስም ለውጥ አድርገው ብቅ ለማለት ይገደዳሉ።ለውጡ ግን የተነሱበትን ዓላማ የሚሽር ሳይሆን ወደዓላማቸው መሳካት የሚያስችላቸው አሳሳች መንገድ መፍጠር ነው።ስለሆነም ሰሞኑን በኦነግ ዙሪያ የሚታየው ትርምስና የሚጨበጨብለት አዲስ መጡ ቡድን ዓላማና አቋም ከዚህ የራቀ አይደለም።ይኸው በነጀነራል ከማል የሚመራው የኦነግ አካል እራሱን ብቸኛ የኦነግ ተጠሪ በማድረግ ለዓመታት ሲያራምደው የነበረውን የመገንጠል ጥያቄ አንስቶ በአንድነት ለአንድነት ለመታገል ተነስቻለሁ፤ከግንቦት ሰባት፣ከጥምርና ከአፋር ነጻ አውጭ ግንባር ጋርም አንድነት በመፍጠር ወያኔን ለመጣል እታገላለሁ ሲል በይፋ መግለጫ አውጥቷል። ሌሎቹ ለአንድነት የሚታገሉ ሃይሎች ለዓላማዬ ስለማይመቹ ግንቦት ሰባትን ለመቀላቀል መርጫለሁ የሚለው ይኸው ቡድን ግንቦት ሰባትን የመረጠበትንና ከሌሎቹ ጋር አብሮ ለመተባበር ያልቻለበትን ነጥብ አላብራራም።በየስብሰባው ላይ እንደሚገልጡት ከሆነ ግን የኦሮሞ ሕዝብ"ራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን መብቱን ለማስከበር" የሚታገሉ መሆናቸውን ሳይደብቁ በአደባባይ ገልጸውታል።በዚህ

ውኸርንብር በሸፈነው አቋማቸው አንዳንዱን ቀና ወገን ለማሳሳትና በደስታ ለማስፈንደቅ ሞክረዋል፤ ችለዋልም። ግን ድጋፉ አብሯቸው አያመሽም።እውነትና ንጋት እያደር ነው እንደሚባለው እውነቱ ሲወጣ አሁን የሰበሰቡት ድጋፍ እንደ ጉም ጥሏቸው ይተናል።ሌላው እራሱን የቻለው ስህተታቸው ደግሞ ኢሳያስ አፈወርቂን የመሰለ የወጣለት ጸረ ኢትዮጵያ የሆነ በሚመራው አገርና መሬት ተቀምጠን ትግል አካሂደን ለኢትዮጵያ የተሻለ ለውጥ እናመጣለን ማለታቸው ነው።የማይመስል ነገር ለወዳጅህ አትንገር የሚባለውን አባባል ቢያውቁት ኖሮ ይህን የመሰለ የጅል አካሄድ ዘዴ ነው ብለው ሊነግሩን ባልደፈሩ ነበር።ዳሩ ያልተደራጀና የተዝረከረከ መቀለጃ ከመሆን አያመልጥምና የሚሉንን እየሰማን እንኖራለን እነሱም በቀልድ ላይ ቀልድ እየነገሩን ይኖራሉ።

ይህ ሰሞኑን የሚናፈሰው ወሬ የአቋም ለውጥ ሳይሆን የአቀራረብ ስልት ለአለፉት ስድስት ወራት በግንቦት ሰባት የስብሰባ አዳራሾች በተደጋጋሚ ላቀረቡት አስተያየት በመግለጫቸው በይፋ እንዲያወጡ ሲነሳና ሲጠየቁበት ለነበረው ጥያቄ መልስ ለመስጠት የሞከሩበት የመጀመሪያ እርምጃ ነው።መሠረታዊ ዓላማው ከአክራሪው የኦነግ አቋም ባይለይም በአቀራረቡ ለስለስ ያለ በመሆኑ የተለዬ ያደርገዋል።ወደ ዘላቂና አስተማማኝ የሕዝቦችና የአገር አንድነት ለመድረስ ግን ብዙ የሚቀረው ነገር አለ። አሁንም የነጻነቱ ጥያቄ ተሸሯል ቢባልም የራሱን ዕድል እራሱ ይወስን በሚለው ሃረግ የተሸፈነ በመሆኑ ግልጽነት ይጎድለዋል።የእራሱን ዕድል እራሱ ይወስን ሲባል ምን ማለት ነው?ውሳኔው ገደብና ልኩ የት ድረስ ነው?በውስጣዊ አስተዳደር፣በግንባታ ሥራ፣በጸጥታና በሰላም ማስጠበቅ ተግባር፣ በመንገድና በልዩ ልዩ ኢንፍራክራክቸርስ ዕቅድና ተግባር፣በቦታ ስምሪት፣ በዳኝነት ሥራ፣በመሳሰሉት የከባቢ እንቅስቃሴዎች ላይ ነው ወይስ መገንጠልንና የነጻ መንግሥት መቋቋምን ይጨምራል?ከፌዴራል አስተዳደሩ ጋር የሚኖረው ግንኙነት ምንና እንዴት ነው።ማን በምን ጉዳይ ላይ የመወሰን ሥልጣን አለው?በከባቢው የተፈጥሮ ሃብት ላይ ወሳኙና ባለቤቱ ማን ነው?የመንግሥት ግብርና የባጀት ጥያቄ በማን ይወሰናል? ከመካከለኛው መንግሥታዊ ተቋማት ጋር የሚኖረው ግንኙነት ምን ይመስላል?በአገሪቱ የመከላከያ ተቋም የሚኖረው ድርሻና ግዳጅ ምን ይመስላል?ለከባቢ ወይስ ለአገር አቀፍ ጥቅምና ልዑልና የቆመ፣ የሁሉንም ደህንነት ሰላምና ያገሪቱን አንድነት በማስጠበቅ ደረጃ የሚዋቀር ሠራዊት ወይስ ለክልል አስተዳዳሪዎች ታዛዥና መከታ የሆነ የታጠቀ ወታደራዊ ሃይል?ከውጭ አገር መንግሥታት ጋር የሚኖረው ግንኙነት በማን ይካሄዳል?እነዚህ ሁሉ መልስ መሰጠት የሚገባቸው ጥያቄዎች ናቸው።

የነጀነራል ከማል ቡድን የወያኔን አንቀጽ 39 ኙን እንደምን ያዩታል?አገራችንን ለመገነጣጠል የተቀመረ ነው ብለው ይቃወሙታል ወይስ በተግባር እንዲገለጽ ይሻሉ?እስከዛሬ ድረስ ግንቦት ሰባትም ቢሆን በዚህ አንቀጽ ላይ ጥርት ያለ አቋም ሲያስተናግድ አልታየም።ነገ ወያኔ በዚህ አንቀጽ መሠረት ብሔሮች መብታችሁን አስከብሩ ብሎ ቢፈቅድ የለም የኢትዮጵያ ሕዝብና የአገር አንድነት በዚህ መልክ አይጣስም፣የኢትዮጵያ ዳር ድንበርና ነጻነት መከበር አለበት ብለው በመቃወም ለመገንጠል የሚሹትን ለመፋለም ይነሳሉ?ከሌላው ቀርቶ ለመገንጠል ከሚሹት የኦሮሞ ድርጅት ነን ከሚሉት ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት ምን ይሆናል?እውነት ለአንድነት

በመቆም ሊቃረኑ ይችላሉ?ወይስ መንገዳችን እንጂ ዓላማችን አንድ ነው ብለው አብረው በመቆም ዕድሉን ይጠቀሙበታል?ይህ እንግዲህ በሚያደርጉት ጉዞና ሂደት የሚታይ ይሆናል።አሁን በደፈናው ይገነጠላሉ ለማለት ባያስችልም አይገነጠሉም ብሎ የሚሉትን ብቻ ተቀብሎ መዝናናት አይገባም።በተጨማሪም በያዙት አቋም የሚያምኑና የሚጸኑ ከሆነ ፣በፊት የሚያራምዱትን የመገንጠል ጥያቄ የሻሩት ከሆነ ከአሁን በኋላ በፊት ጊዜ ይጠሩበት የነበረውን "ኦነግ" የሚለውን ስማቸውን በሌላ ህብረትንና ኢትዮጵያዊነትን በሚያንጸባርቅ ስም መለወጥ ይኖርባቸዋል። ምክንያቱም ለመገንጠልና ለነጻነት የሚታገሉ ሳይሆኑ ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ሥርዓት መስፈን ለመታገል ተነስተናል ብለዋልና ያ መጠሪያ አሁን ይዘናል ከሚሉት ዓላማ ጋር የሚስማማ አይደለም።

በተጨማሪ የግንቦት 7 እንቅስቃሴና ተባባሪዎቹ ትግል ወያኔን በመጣል ላይ ብቻ ያተኮረና የተወሰነ መሆኑን ደጋግመው ስለገለጹ አቋማቸውን አስተካክለውና አርመው ከወያኔ መወገድ ጋር አብሮ መደረግ ያለበትን ትልቁን ሥራ ማለትም አገሪቱ በዲሞክራሲ ስርዓት ሥር የምትተዳደርበትን ፣የውጭና የውስጥ ጠላቶችን በመቋቋም የኢትዮጵያ ዳር ድንበር ተከብሮ የምትኖርበትን  ዕድልና መንገድ ለመፍጠር ከሚሹትና ከሚችሉት ሃይሎች ጋር የግዴታ የአንድነት ግንባር ፈጥሮ መታገል ይኖርባቸዋል።የወያኔ መውደቅ ብቻውን ለሕዝቡና ለአገሪቱ ብሩህ ተስፋና ለውጥ አያመጣም።ሌሎቹን አግልሎ በአንድና ሁለት ድርጅቶችና በውጭ ሃይሎች ድጋፍ የሚመጣ ለውጥ አንዱን በአንዱ ከመተካት በስተቀር ሥር ነቀል ለሆነ ሕዝባዊ ለውጥ አያበቃም።ለውጡ ለውጭ ሃይሎች  የሚመች የፈረስ ለውጥ ይሆናል።ሥር ነቀል ለውጥ ለማምጣት የሁሉም ኢትዮጵያዊ የጋራ ፍላጎት የሚንጸባረቅበት ፣ከሁሉም የተውጣጣ ዴሞክራቲክ የሆነ የጋራ ግንባር የሚመራው ትግል ሲካሄድና የሽግግር መንግሥት ተቋቁሞ በተረጋጋ ሁኔታ በሕዝቡ ምርጫና ውሳኔ ቋሚ መንግሥት ሲመሠረት ብቻ ነው።አለያ አልሸሹም ዘወር አሉ ይሆናል።

ለተሻለ መግባባትና መቀራረብ ሁሉም የሚሰማውን ሳይፈራና ሳይቆጥብ አውጥቶ መናገር፣መጻፍ ይኖርበታል።በፍርሃትና በይሉኝታ የማይፈልጉትን ሳይቃወሙ ማሳለፍ የጥፋት ተባባሪ መሆን ነው።

በየአቅጣጫው የሚሰነዘረውን ሃሳብና አስተያየት ማሰማትና ማሰራጨት ከሀቀኛና ነጻ አምድ አዘጋጆችና ድህረገጽ ተቋማት ይጠበቃል።ሃሳብ እንዳይንሸራሸር ማፈንና በሳንሱር ማገድ የነጻ ፕሬስን ዓላማና ጸባይ መጣስ ነው።

የተቃውሞ ሃሳብና አስተያየት የተሰነዘረባቸውም ቢሆኑ ለቀረበባቸው ትችት ተገቢ መልስና ማብራሪያ መስጠት ይገባቸዋል እንጂ በዛቻና በማስፈራራት ወይም ቅጥያ ስም በመስጠትና በመለጠፍ ስብእናን መንካት የወራዳ ተግባር መሆኑን ሊገነዘቡት ይገባል። መሪነት የችሎታ፣የትግዕስትና የሀቅ ባለቤትነትን የሚጠይቅ ሙያና አደራ እንደሆነ በቅድሚያ ሊገነዘቡት ይገባል።በዚያ በዚህ ሸውጀና አስፈራርቼ፣በድብቅ የምፈልገውን አደርጋለሁ ፣አገኛለሁ ማለት ጊዜ የረሳው ሞኝነት ነው።ዘመኑ የመረጃ  (የኢንፎርሜሽን) ምንጭ በብዛት የፈለቀበት ጊዜ ነው።መጋለጥ አይቀርም።

የአገራችንን ሰላም አንድነትና የዲሞክራሲን ሥርዓት መስፈን ፣የሰብአዊ መብትን መከበርና የወያኔን ዘረኛ መንግሥት መወገድ የምንሻ ከወሬና ከምኞት አልፈን ፍላጎታችንን በተግባር ለማየት በምንችልበት መንገድ መሰባሰብና መምከር ይኖርብናል።ጊዜው የተግባር እንጂ የቃል ብቻ አይደለም።ስለሆነም በአንድነት ሃይል ስም የተሰባሰበው ያቀረበውን ጥሪ ተቀብለን ለአንድነት ግንባር ምሥረታ የሚያበቃ ጉባኤ እንዲሳካ በአካል፣በሃሳብና በማተሪያል ማገዝ ይኖርብናል።ያልተደራጀው ይኸው የአንድነት ሃይል የሆነው ብዙሃን ተደራጅቶ ሃይሉን ማሳየትና ድምጹን ማሰማት ይኖርበታል። ያ ካልሆነ ግን ሰሚ የሚኖረው የብዙሃን ድምጽ ሳይሆን የተበታተነ ጫጫታ ይሆንና ካለፈው በባሰ ውድቀትና ጸጸት ውስጥ እንወድቃለን።መሳቂያ መሳለቂያ እንሆናለን።

የያዝነው ዓመት የህብረትና የድል እንዲሆንልን እመኛለሁ

አገሬ አዲስ